09

ምዕራፍ

4ኛ ዓመት ቁጥር 40
4th year Nº. 40



ባህር ዳር ጳጉሜ 1 ቀን 1991ዓ.ም
Bahir Dar 6th Sep., 1999

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

ዝክረ ሕግ
ZIKR HIG

OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE
IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

የአንዱ ዋጋ ብር 2.45	በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ	የፖ.ሣ.ቁ 312 P.O.BOX

ማ ው ጫ	CONTENT
አዋጅ ቁጥር 40/1991 የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኅብረት ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ ቢሮን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ገጽ 8	Proclamation Nº 40/1999 A Proclamation That Provides For The Establishemnt Of Coopratives Promotion Bureau Of The Amhara National Regional State page 8

አዋጅ ቁጥር 40/1991
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኅብረት ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ ቢሮን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

በአማራ ብሄራዊ ክልል ተመሣሣይ ፍላጎት ባላቸው ሰዎች መካከል በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ኅብረት በመፍጠር ገንዘብን፣ ዕውቀትን ፣ ንብረትንና ጉልበትን በማስተባበር ቁጠ ባንና እርስ በርስ መደጋገፍን የሚፈጥሩ

PROCLAMATION Nº 40/1999
A PROCLAMATION THAT PROVIDES FOR THE ESTABLISHEMENT OF COOPRATIVES PROMOTION BUREAU OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE.

WHERE AS, it has become necessary to establish cooperatives among individuals having similar needs on voluntary bases by pooling their finance, knowledge and property which bring saving and mutual assistance in the Amhara National

የኅብረት ሥራ ማህበራትን ማቋቋምና ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮቻቸውን እንዲፈቱ ማድረግ አስፈላጊ ስለሆነ፤

አባላት በማህበራቸው አማካኝነት ምርትን ለማሣደግ የሚያስችሉ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን፣ የኢንዱስትሪ ውጤቶችንና የብድር አገልግሎት እንዲያገኙና በነጻ ገበያ ተወዳድረው ምርታቸውን ወይም አገልግሎታቸውን በተሻለ ዋጋ ለመሸጥ የሚያስችላቸውን ሁኔታ በማመቻቸት ለክልሉ ልማት ተገቢውን ሚና እንዲጫወቱ ማድረግ በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በወጣው የኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 147/1991 መሠረት ለተቋቋሙና ወደፊትም በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚቋቋሙ ማህበራት ድጋፍ የሚሠጥ፣ የኅብረት ሥራ ማህበራትን የሚያስፋፋና የሚያስተባብር አንድ የመንግሥት አካል ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ፤

የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ም/ቤት በክልሉ ህገ መንግሥት አንቀጽ 49/3/1 መሠረት የሚከተለውን አውጇል።

ክፍል አንድ
ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ
   ይህ አዋጅ "የአማራ ብሄራዊ ክልል የኅብረት ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ ቢሮ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 40/1991" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።
2. ትርጓሜ
   የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፤
   1."ማህበር" ማለት በአዋጅ ቁጥር 147/1991 መሠረት የተደራጁና የተመዘገበ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ነው። በተለይም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ይጨምራል።
   ሀ.የገበሬዎች የኅብረት ሥራ ማህበራት፣
   ለ.የመኖሪያ ቤት የኅብረት ሥራ ማህበራት፤
   ሐ.የኢንዱስትሪና የዕደ ጥበብ የኅብረት

Region, and cause to enable to solve their social and economic problems.

WHERE AS, it has become essential to facilitate conditions, by which through their cooperatives the members can get modern agricultural technologies, industrial products and credit services that enable to develop productions and competing in the free market economy sell their production or services with a better price. And play the appropriate role for the development of the region.

WHERE AS, it has been found essential to establish government organ which can support, promote and coordinate agricultural cooperatives which have been established pursuant to cooperatives establishment proclamation № 147/1998 that has been proclaimed by democratic republic of Ethiopia and cooperatives to be establish according to this proclamation.

NOW, THERE FORE, the council of the Amhara National Regional State pursuant to sub article 3/1 of article 49 of the constitution of the region is here by proclaimed as follows.

PART ONE
GENERAL

1. Short Title
This proclamation may be cited as "The Amhara National Region cooperatives promotion Bureau establishment proclamation № 40/1999."

2. Definition
In this proclamation, unless the context otherwise requires:

1."Society" means any cooperative which is established and registered in accordance with proclamation № 147/1998 and it shall in particular include the following:
a. Agricultural cooperative societies,
b. Housing cooperative societies,
c. Industrial and Artisans producers

298

298

ሥራ ማህበራት፣
መ.የቨሜችች የኅብረት ሥራ ማህበራት፣
ሠ.የገንዘብ ቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማህበራት፣
ረ.የዓሣ አስጋሪዎች የኅብረት ሥራ ማህበራት፣
ሰ.የማዕድን የኅብረት ሥራ ማህበራት እና ሌሎችም::

2."የኅብረት ሥራ ማህበር" ማለት ሰዎች በፈቃደኝነት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮቻቸውን በጋራ ለመፍታት የሚያቋቁሙትና ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የሚያስተዳድሩት መሠረታዊ ወይም ከፍተኛ ደረጃ ማህበር ነው::

3."ክልል" ማለት የአማራ ብሄራዊ ክልል ነው::

4. "መንግሥት" ማለት የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ነው::

5. "ቢሮ" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋመ የኅብረት ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ ቢሮ ነው::

ክፍል ሁለት
ስለ ቢሮው መቋቋም፣ ተጠሪነት፣ የቢሮው አደረጃጀትና ዓላማዎች

3. ስለ ቢሮው መቋቋምና ተጠሪነት

1.የአማራ ብሄራዊ ክልል የኅብረት ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ ቢሮ ከዚህ በኋላ «ቢሮው» እየተባለ የሚጠራ ራሱን የቻለ እና ህጋዊ ሰውነት ያለው የመንግሥት መ/ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል::

2. ቢሮው ተጠሪነቱ ለአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴና ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ይሆናል::

4. የቢሮው መዋቅራዊ አደረጃጀት

1. ቢሮው በክልሉ የሚሾም የቢሮ ኃላፊ፣ም የቢሮ ኃላፊና ለሥራው የሚያስፈልጉ ሌሎች ሠራተኞች ይኖሩታል::

2.የቢሮው ዋና መ/ቤት ባህር ዳር ከተማ ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ በዞንና በወረዳ የሚቋቋሙ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ይኖሩታል::

5. የቢሮው ዓላማዎች

ቢሮው የሚከተሉት ዓላማዎች

cooperative societies
d. Consumers cooperative societies
e. Savings and credit cooperative societies
f. Fishery cooperative societies,
g. Mining cooperative societies and others

2."Cooperative society " means a primary or high society established on voluntary bases and managed democratically by individuals to collectively solve their economic and social problems.

3."Region" means the Amhara National Region

4."State" means the Amhara National Regional State.

5. " Bureau" means cooperative promotion Bureau established in accordance with this proclamation.

PART TWO
Establishment, Accountability, organization and objective of the Bureau

3. Establishment and Accountability

1.The Amhara National Region cooperative promotion Bureau here in after referred to as "the Bureau" is here by established as an autonomous body having its own legal personality pursuant under this proclamation.

2.The Bureau is accountable to the executive committee and the Head of the Regional state.

4. Organizational structure

1. The Bureau shall have the head and deputy head of the Bureau to be assigned by the region and other necessary staffs.

2. The head office of the bureau shall be in Bahir Dar and may establish branch offices in different zones and woredas as may be necessary.

5. Objectives of the Bureau

The Bureau shall have the following

ይኖሩታል::

1.ለክልሉ ሕዝብ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ የሚያስገኙ በአባላቱ ፍላጎት ላይ የተመሠረቱ የተለያዩ ዓይነት የኅብረት ሥራ ማህበራት እንዲደራጁ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር፤

2.ምርትና ምርታማነትን ለማሣደግ የሚያስችሉ ግብዓቶችንና ለኑሮ የሚያሰፈልጉ ሸቀጣ ሸቀጦችን፣ ምርቶችንና አገልግሎቶችን ማህበራት እንዲያገኙ አገዛ ማድረግ፤

3.የኅብረት ሥራ ማህበራት የምርት ውጤቶችን ከአባላት በመግዛትና ለገቢያ በማቅረብ የአባሎቻቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ በሚያደርጉት ጥረት ተገቢውን ድጋፍ መስጠት፤

4.ማህበራት በነጻ ገበያ ኢኮኖሚ ውስጥ ብቁ ተወዳዳሪ ሆነው የራሳቸውን ችግር ከመፍታት ባሻገር ለክልሉ ልማት ጉልህ ተሣትፎ እንዲኖራቸው የማህበራቱን አቅም ለመገንባት የሚያስችሉ ተከታታይ ስልጠናዎችና ሌሎች ሁለንተናዊ ድጋፎችን ማድረግ::

ክፍል ሶስት
የቢሮው እና የቢሮ ኃላፊው ሥልጣንና ተግባር

6. የቢሮው ሥልጣንና ተግባር

ቢሮው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፤

1.የኅብረት ሥራ ማህበራትን በሚመለከት የፖሊስ ሃሣቦች ያመነጫል፣ የጥናትና የምርምር ተግባራትን ያከናውናል፤ ለኅብረት ሥራ ማህበራት እድገት የሚጠቅሙና በአባላት ተሣትፎ የሚሠሩ የልማት ፕሮጀክቶችን ያዘጋጃል፤ የአፈጻጸም ስትራቴጂና ቅደም ተከተል ያወጣል፤ ሲፀድቅም በተግባር ያውላል::

2.የኅብረት ሥራ ኤክስቴንሽንን በገጠሩና በከተማ ለማስፋፋትና ለማዳበር የሚያስችሉ ተከታታይ የትምህርትና የሥልጠና ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት ለኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት፣ ለማህበራት ቅጥር ሠራተኞችና ለኅብረት ሥራ ባለሙያዎች ይሠጣል::

3.በአባላት ፍላጎት መሠረት ማኅበራት እንዲደራጁ አስፈላጊውን እገዛ

objectives to:

1.Facilitate conditions for the organization of different kinds of co-operatives based on the interest of their members, which may bring socio-economic benefit for the people of the region.

2. Support cooperatives so that they can get modern inputs that enables to improve production & productivity, and other commodities, productions & services necessary for life.

3. Render the appropriate support for cooperatives in their effort to secure the benefit of their members by buying & marketing their products.

4.Provide continuing training and other all-round support which enable cooperatives solve their problems and be formidable competitor in the free market economy and strengthen their participation in the development of the region.

PART THREE
Powers And Duties Of The Bureau And The Bureau Head

6. Powers and Duties of the Bureau

The bureau shall have the following powers & duties to:

1. Initiate policy issues concerning cooperatives in the region, conduct study and research activities, prepare development projects essential for the growth of cooperatives to be implemented through the participation of members, issue implementation strategy respectively and upon approval implement the same.

2.Prepare and render continuing education and training programs for members of cooperatives, employs and experts of cooperatives, which enable to promote and strengthen cooperative extensions in the rural and urban areas.

3.Render the necessary support to organize different types of cooperatives based on

ያደርጋል፤

4.አባላት በኅብረት ሥራ ማህበራቸው በኩል የምርት ማሣደጊያ ግብዓቶችን፣ የምርት ውጤቶችን፣ አገልግሎቶችን፣ በጥናት ላይ የተመሠረተ ብድር እንዲያገኙና ምርትንና አገልግሎትን በተሻለ ዋጋ በመሸጥ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

5.ማህበራት አስፈላጊና ወቅታዊ የገበያ መረጃ እንዲያገኙ በማድረግ በነጻ ገበያ ተወዳዳሪ ሆነው ተጠቃሚ የሚሆኑበትንና ለክልሉ የኢኮኖሚ ዕድገትም ተገቢውን አስተዋጽኦ የሚያደርጉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

6.አለም አቀፍ የኅብረት ሥራ መርሆዎችን መሠረት በማድረግና የክልሉን ተጨባጭ ሁኔታ በማገናዘብ በአዋጅ ቁጥር 147/1991 መሠረት የተደራጁ ማህበራትን ይመዘግባል፣ የህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ ሠርቲፊኬት ይሰጣል፣ ይሠርዛል::

7.በክልሉ ውስጥ ከፍተኛ ደረጃ የኅብረት ሥራ ማህበራት እንዲቋቋሙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

8.የኅብረት ሥራ ማህበራት በሚዋሀዱበት፣ በሚለያዩበት ፣ ወይም በሚፈርሱበት ጊዜ በፌዴራል መንግሥት በወጣው አዋጅ ቁጥር 147/1991 መሠረት እንዲፈፀም አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል::

9.የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሣብ አያያዝና የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት እንዲጠናከር የሙያ እገዛ በመስጠት ገንዘብና ንብረታቸው እንዳይባክን ጥረት ያደርጋል፣ ወቅታዊ የሂሣብ ምርመራ በማካሄድ ያግዛል፤

10.ቢሮው በሚያደርጋቸው የሂሣብ ምርመራ በማኅበራት ገንዘብና ንብረት ላይ ጥፋት መድረሱን ካመነ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር እንዲመለስ ጥረት ያደርጋል፤ ተገቢውን ህጋዊ እርምጃ ለማስወሰድ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

11.የኅብረት ሥራ ማህበራትን የሚመለከቱ ህጐች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች በትክክል በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

the interest of their members.

4.Facilitate conditions by which members through their cooperatives get modern technologies that are necessary for the improvement of their productions, industrial products, study-based credit and benefit by selling their productions with a better price.

5.Facilitate conditions for cooperatives to compete in the free market economy by making available timely market information, so that they can be benefited and thereby contribute in the economic development of the region.

6.Register and issue certificate of legality to cooperatives organized based on the international cooperative principles, taking in to account objective conditions of the region and in line with the federal proclamation Nº 147/1998.

7. Facilitate conditions for the establishment of high level cooperatives in the region.

8/ Render the necessary support and follow up the amalgamation, division or dissolution of cooperatives to be in line with the federal state cooperative proclamation Nº 147/1998.

9. Exert an effort to contain the misuse of finance and property of cooperative societies by giving professional support for the strengthening of their accounting and inspection system; and support by auditing their accounts timely.

10.Exert an effort for the reinforcement incorporation with the concerned bodies where it believes there is an embezzlement of finance and property of cooperatives through its financial auditing. Facilitate conditions for the appropriate legal action to be effected.

11.Follow up and supervise the proper execution of laws, regulations and directives concerning cooperatives.

12.የቢሮውን ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፤ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤
13.የንብረት ባለቤት ይሆናል፤ ውል ይዋዋላል፤ በስሙ ይከሣል፤ ይከሰሳል፤
14.ቢሮውን በሚመለከት ረቂቅ ህጐችንና ደንቦችን ለአማራ ብሄራዊ ክልል ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አቅርቦ ያስፀድቃል፤ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፡

15.ዓላማውን ለማስፈፀም የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

7. <u>የቢሮ ኃላፊው ሥልጣንና ተግባር</u>

የቢሮ ኃላፊው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ላይ ለቢሮው የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት የሚያከናውን ሲሆን፤ በተጨማሪ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡

1.የቢሮውን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል።
2.የቢሮውን የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ዕቅድ የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤
3.በመንግሥት ሠራተኞች አስተዳደር ህግ መሠረት ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሠናብታል፤
4.ለቢሮው በተፈቀደው በጀት፣ ሥራና ዕቅድ መሠረት የገንዘብ ክፍያ ይፈጽማል፤
5.በህግ መሠረት በቢሮው ስም የባንክ ሂሣብ ይከፍታል፣ ያንቀሳቅሣል፤
6.እንደአስፈላጊነቱ በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር ለቢሮው ሠራተኞች በውክልና ይሰጣል፤
7.የቢሮውን ድርጅታዊ መዋቅር አጥንቶ ለክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ያቀርባል፤ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤
8.ስለ ሥራው አፈጻጸም በየጊዜው ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያቀርባል፤
9.ቢሮው ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርገው ግንኙነት ሁሉ ጽ/ቤቱን ይወክላል፤
10.በክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴና በርዕሰ መስተዳድሩ የሚሰጡትን ለሎች ተመሣሣይ ሥራዎች ይፈጽማል።

12.Prepare plan and budget of the Bureau and up on approval implement the same.
13. Own property, enter into contract, sue and be sued, in it's own name.
14.Prepare and submit for approval draft laws, directives concerning the Bureau to the executive committee of the Amhara National Regional State and upon approval implement the same.
15. Perform such other activities necessary for the execution of its objectives.

7.Powers And Duties Of The Head of The Bureau

The Bureau head shall, in addition to the powers and duties given to the Bureau under article 6 of this proclamation, have the following powers and duties to:

1.Direct, administer and supervise the activities of the Bureau.
2.Prepare and submit short, medium and long term plan, annual action plan and budget of the Bureau and implement the same upon approval.
3. Employ, administer and dismiss the necessary employees in accordance with civil service regulations.
4. Effect payments based on the approved work plan and budget of the Bureau.
5.Open and operate bank accounts in the name of the Bureau in line with laws.
6.Delegate his power and duty to staffs, when necessary.
7.Study and submit, organizational structure of the Bureau to the Regional executive committee, and implement the same upon approval.
8.Submit periodic reports to the concerned body.
9.Represent the Bureau in its dealings with other third parties.
10. Perform such other activities as assigned to it by the executive committee and Head of the regional

ክፍል አራት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

8. ዕለ በጀትና የሂሣብ መዛግብት

1.የቢሮው የገንዘብ ምንጭ መንግሥትና ሌሎች ይሆናሉ፣

2. ቢሮው የተሟላና ህጋዊ የሆነ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል።

3. የቢሮው የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሠነዶች በክልሉ ዋና አዲተር ወይም እሱ በሚሠይማቸው አዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ።

9. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

1.በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት አዋጅ ቁጥር 25/1990 መሠረት ተቋቁሞ ለነበረው የገበሬዎች ጎብረት ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ ጽ/ቤት ተሰጥቶት የነበረው ሥልጣንና ኃላፊነት በዚህ አዋጅ መሠረት ለተቋቋመው ቢሮ ተላልፏል።

2. በተመሣሣይ ከዚህ በፊት የተለያዩ የጎብረት ሥራ ማህበራትን ለማደራጀትና ለመመዝገብ ለሌሎች ቢሮዎች ተሠጥቶ የነበረው ሥልጣንና ኃላፊነት በዚህ አዋጅ መሠረት ለነበረት ሥራ ማህበራት ማስፋፊያ ቢሮ ተላልፏል።

10. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ጉዳዩ የሚመለከተው አካል ሁሉ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች በሥራ ላይ እንዲውሉ የመተባበር ግዴታ አለበት።

11. ተፈጻሚነት የሌላቸው ህጐች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ህግ በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

12. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ቢሮው ይህን አዋጅ በሚገባ ሥራ ላይ ለማዋል የሚረዱ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

13. አዋጁን የማሻሻል ሥልጣን

ይህ አዋጅ ሊሻሻል የሚችለው በክልሉ ም/ቤት ብቻ ነው።

14. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

State.

PART FOUR
Miscellaneous Provisions

8. Budget and Books of Accounts

1. The source of income of the Bureau shall be the government and other sources.
2. The Bureau shall keep appropriate and complete books of accounts.
3. The books of accounts and financial documents of the Bureau shall be audited every year by the auditor General or other auditors to be assigned by it.

9. Transitory Provisions

1.All powers and responsibilities vested to the office of agricultural cooperatives promotion office established pursuant to the Amhara National Regional State proclamation N^{o} 25/1998 are here by transferred to the Bureau established under this proclamation.

2. All powers and responsibilities which were previously vested to other bureaux , to organize and register different cooperative societies, are here by similarly transferred to cooperatives promotion bureau pursuant to this proclamation.

10. Duty to Cooperate

Any concerned organ shall have a duty to cooperate in the execution of the provisions of this proclamation.

11. In Applicable Laws

Any Law that is inconsistent with this proclamation shall not apply with respect to matters provided for here in.

12. Power to Issue Directives

The Bureau may issue directives for the proper implementation of this proclamation.

13. power to amend the proclamation

This proclamation can only be amended by the Regional council

14. Effective Date

ይህ አዋጅ በአማራ ራሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

ባህር ዳር
ጳጉሜ 1 ቀን 1991 ዓ.ም
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት

This proclamation shall come in to force from the date of its ratification by the council of the region.

Done at Bahir Dar
This 6th day of Sept., 1999.
Council of the Amhara National Regional State.

304

304